NMA ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ
NATIONAL METEOROLOGY AGENCY

# የአስር ቀንና ወርሃዊ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 1-31/2021 የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከአፕሪል 1-30/2021 የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

አፕሪል 2021
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ 3

ካርታ 6 ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 4

ካርታ 7 ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........ 5

ካርታ 8 ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... 6

እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........ 7

እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........ 8

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........ 8

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ........ 9

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........ 10


## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ ማርች ወር በመጀመሪያዉና ሶስተኛዉ አስር ቀናት በአንዳንድ የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረዉ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ በስተቀር አብዛኛዉን ጊዜ ፀሃያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ነበር የሰነበተዉ፡፡ በሌላ በኩል በሁለተኛዉ አስር ቀናት ላይ እርጥበታማዉ የአየር ሁኔታ ወደ ሀገራችን በመግባቱ አብዛኛዎቹ የምዕራብና ደቡብ እንዲሁም ጥቂት የደቡብ ምስራቅ፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በነኚህ ቦታዎች ላይ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የማርች ወር ምዕራብና መካከለኛዉ አማራ፣ ምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የሲዳማ ክልል፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ ሱማሌ፣ የመካከለኛዉና ምስራቅ ሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በደቡብ አማራ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በደቡብና ምዕራብ ኦሮሚያ ጥቂት ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በደብረወርቅ 30.0፣ በአማን 30.3፣ በጋምቤላ 30.6፣ በአርጆ 32.4፣ በያቤሎ 42.4፣ በጊንር 66.0፣ በማጂ 59.8፣ በበደሌ 51.8፣ በአቦቦ 41.5ና 43.5 በሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፈዉ የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ ክልል በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ጎንደር ምስራቃዊው ክፍል፣ በደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅና ምእራብ ጎጃምና በአገዋዊ፤ በቤንሻንጉል ጉምዝ፤ በሁሉም የጋምቤላ ዞኖች፤ በአብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከኦሮሚ በምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ፣ በጂማ፣ በባሌ፣ በጉጂና ቦረና፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ እንዲሁም ከሶማሌ በፋፈንና በቆራኼ ዞኖች ላይ ከ-188 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-19 ቀናት ያህል ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7) ፡፡

ባለፈዉ የማርች ወር የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር የአሶሳ፤ የጋምቤላ ሁሉም ዞኖች፤ የኢሉአባቦራ እና የምዕራብ ወለጋ ዞኖች ከእንዲሁም ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የቤንች ማጂ፣ የከፌቾና የሲዳማ ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቃማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ቆይተዋል (ካርታ 8) ።


ካርታ 6   ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7   ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 8   ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ወር በመጀመሪያዉና ሶስተኛዉ አስር ቀናት በአንዳንድ የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረዉ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት በስተቀር አብዛኛዉን ጊዜ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ በሌላ በኩል በሁለተኛዉ አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የምዕራብና ደቡብ እንዲሁም ጥቂት የደቡብ ምስራቅ፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አንስተኛ እርጥበት ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የማርች ወር በምዕራብና በመካከለኛዉ አማራ፣ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ ክልል፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ሱማሌ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ ሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የነበራቸዉ ሲሆን ይህም ሁኔታ በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖራቸው ያስቻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የማሳ ዝግጅት ለማድርግ እና የተለያዩ ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚበቅሉ ቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በጎ ጎን ነበረው። በተጨማሪም ከከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በደቡብ፤ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በደቡብና ምዕራብ ኦሮሚያ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የነበረ ሲሆን፤ የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ውኃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውኃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት ጥሩ ጎን ነበረዉ፡፡ በሌላ በኩል በልግ ተጠቃሚ በሆኑት በተለይም በሰሜን ምስራቅ፤ በመካከለኛዉና በምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን በወቅቱ የበልግ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ለሚያከናዉኑ አካባቢዎች፣ ለአፈር እርጥበት፤ ለዘር መዝራት፤ ለአረንጓዴ ተክሎች ልምላሜና ለጓሮ አትክልት እንዲሁም ለእንሰሳት የመጠጥ ውሃና የመኖ አቅርቦት አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረዉ (ካርታ 9) ፡፡


ካርታ 9 ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-31 ማርች 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ በጥቂት የታችኛዉ አባይ፣ የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ እና ገናሌዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ የተቀሩት አብዛኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ኦጋዴን፣ አዋሽ፣ አባይ፣ ተከዜ እና አፋርደናከል ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሗል፡፡

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል ከዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር ጋር ተያይዞ፤ ከተቀሩት የበልግ ወራት አንጻር በጎላ መልኩ የዝናብ መጠንና ሥርጭቱ በብዙ ሥፍራዎች ላይ የሚጠናከርበትና የሚስፋፋበት ወር ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለጎርፍ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ከኦገስት ወር ጀምሮ ያለፉት የበልግ ሁለት ወራት የፓስፍክ ዉቅያኖስ ምስራቃዊና መካከለኛዉ ክፍል የዉሃ አካል ከመደበኛ በታች መቀዝቀዝ (ENSO-LA NIÑA) ተፅእኖ ስር የቆዩ ቢሆንም፣ አሁን ወደ መደበኛዉ ፌር (ENSO-neutral) እንደተመለሰና በቀጣይም በበልግ ወራቶች ቀጣይነት እንደሚኖረዉ የአለም አቀፍ የትንበያ ማእካላት መረጃ ያስረዳል፡፡ ላኒና (ENSO-LA NIÑA) በበልግ ወቅት የዝናብ ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳለዉ የተለያዩ የጥናት ዉጤቶች የሚያስረዱ በመሆኑ ግንዛቤ መዉሰድ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በመጪው ኤፕሪል ወር ለዝናብ መፈጠር አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከቀን ቀን እየተሻሻሉ በመሄድ በአመዛኙ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል። ይሁንና ከበልግ ዝናብ የመዋዡቅ ባህርይ ጋር ተያይዞ በወሩ ውስጥ ደረቃማ ቀናት ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

በመሆኑም ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ፣ ምእራብ እና ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቦሌና አሪሲ፣ ቦረናና ጉጂ፤ ከጋምቤላ ክልል የኣኝዋክና የመዠንግር ዞኖች፤ ሁሉም የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የመካከለኛ ዞኖች፤ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የቤንች ማጂ፣ ጥቂት የከፋ እና ኮንታ ዞኖች፣ የደቡብ ኦሞ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የማግኘት እድል ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማርም የአፋርና የሱማሌ ክልል ዞኖች፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ ፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው በታች ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኤፕሪል ወር የእርጥበት ሁኔታው በበልግ አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች የሚስፋፋበትና የሚጠናከርበት ሲሆን፤ ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥበት ወቅት ነው፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች ጎርፍ የሚከሰትበትና እንዲሁም ለዘር በተዘጋጁና በሰብል በተሸፈኑ ማሳዎች ለይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልበት ወቅት ነው፡፡በተሰጠው ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የአፕሪል ወር የእርጥበት ሁኔታው ከቀን ወደ ቀን እየተሻሻለ በመሄድ እንደሚጠናከርና በአመዛኙ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያ ደረጃ ላሉም ሆነ ለቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ጥሩ አስተዋጽኦ ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትም ሆነ በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የሚጠበቅ በመሆኑ አርሶ አደሮች ከወዲሁ ዝግጅት ሊያደረጉ ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አረብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ መልኩ ከበልግ ዝናብ የመዋዠቅ ባህርይ የተነሳ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በወሩ ውስጥ ደረቃማ ቀናት ሊከሰት እንደሚችል በመገንዘብ እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን ውኃ ማጠራቀምና በመሀል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

**ኤፕሪል** ወር ከቀደሙት ፌብርዋሪ እና ማርች ወራት የተሻለ እርጥበት መጠን በምዕራብ በመካከለኛዉና በደቡባዊ አጋማሽ የሀገሪቱ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ በአንፃራዊ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው የትንቢያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህም መሰረት አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ አባይ፣ ገናሌዳዋ፣ ኦሞጊቤና ስምጥሸለቆ፣ የታችኛውና የመካከለኛው ተከዜ፣ የላይኛው አዋሽ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው አፋርደናከልና ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች በአብዛኛው እርጥበታማና በጥቂት ቦታዎች ደግሞ የተሻለ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛው ተከዜ፣ ደቡባዊ አባይ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ እና የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤና ስምጥሸለቆ አዋሰኝ ተፋሰሶች ላይ አነሰተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የበልግ እርጥበት ለወራጅ ውሃ ያለው አስተዋፆ አነስተኛ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሱት ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው እርጥበት የከባቢ አየርን በማቀዝቀዝና በተወሰነ መጠን በአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖር አስተዋፆ ያደርጋል። ይህም ሁኔታ ለገፀምድርና ለከርሰምድር ውሃ ሀብት ዘርፍ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል።